# የሹአ የቅዱሳን መፃህፍት ማህበር



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# ምሥጢራት

# ፭. ምሥጢረ ጥምቀት

በማመን ለሚገኘው ጸጋ ሁሉ በር ነው።

1) ለመዳን፣ ለሥርየተ ኃጢአት

“ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።” ማር. 16፡16

“ ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፣ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፡- ወንድሞች ሆይ፣ ምን እናድርግ አሏቸው። ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ . . . ” የሐዋ. 2፡37-38

- “ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍሳት በውኃ የዳኑበት የመርከብ መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትሥግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፣ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፣ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤ … ”

1 ጴጥ. 3፡20-21

# 2) ለልጅነት

“እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና መንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።” ዮሐ. 3፡5

“አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።

- ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን” ሮሜ 8፡15
- “ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብለችሁ ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ሰጣችሁ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፣ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።”

ገላ. 4፡6-7

# 3. ከክርስቶስ ከሞቱና ከትንሣኤው ለመሳተፍ

- “ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

- “ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን”

ሮሜ 6:3-5

# 4) ክርስቶስን ለመልበስ

“ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።” ገላ. 3፡27

5) ለሀብታት ለምሥጢራት በር ነው።

# ምሥጢረ ጥምቀት በአበው ትምህርት

- “ . . . ክርስቶስ ከመስቀሉ ወርዶ በፊታችን ወደሚታየን ወደሚቀበርበት ቦታ እንደ ተወሰደ አንተም ከእነዚህ ነገሮች በኋላ አምላካዊ የሆነው የጥምቀት ምስጢር ወደሚፈጸምበት ወደ ተቀደሰው የውኃ ገንዳ (Baptismal Font) እንድትሄድ ሆንህ፣ እያንዳንዳችሁም በስመ አብ በስመ ወልድ በስመ መንፈስ ቅዱስ ስለ ማመናችሁ ተጠየቃችሁ። እናንተም ማመናችሁን መሰከራችሁ፣ ወደ መጠመቂያው ውኃም ሦስት ጊዜ እየገባችሁ ወጣችሁ፤ በዚህም ክርስቶስ በመቃብሩ ሦስት ቀን መቆየቱን እየመሰከራችሁ ነው።

- “መድኃኒታችን በልበ ምድር ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንዳሳለፈ እናንተም በመጀመሪያው ከውኃው በመውጣታችሁ ጌታችን በመሬት ውስጥ ያሳለፈውን የመጀመሪያውን ቀን ያመለክታል (ይገልጻል)፤ ወደ ውኃው በመውረዳችሁ ደግሞ በከርሠ ምድር ያሳለፈውን ሌሊቱን ያመለክታል (ይገልጻል)፤ በሌሊት ያለ ሰው እንደማያይ፣ በቀን ያለ ግን ማየት እንደሚችል እንዲሁም ወደ ውኃው በመውረድ ጊዜ እንደ ሌሊቱ ምንም አላያችሁም፤ ከውኃው በወጣችሁ ጊዜ በቀን የሚመላለስ ማየት እንዲችል እናንተም እንደዚሁ ነበራችሁ።” ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት

- “ጥምቀትን ለሥርየተ ኃጢአት ሰጠን፣ እንዲሁም በዚሁ በጥምቀት ከፍዳ እንድንድን፣ መንግሥቱን እንድንወርስ፣ እና መልካም የሆነውን ነገር ብናደርግ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ጥሩ ነገሮች ተስፋ አድርጎ ሰጠን፣ እጁን ዘረጋልን፣ መንፈሱንም በልባችን አፈሰሰልን።”

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ

- “የመጠመቂያውን ውኃ ተራ ውኃ አድርገህ አትመልከተው፣ በውኃው አማካይነት የሚሰጠውን መንፈሳዊ ጸጋ እንጂ። . . . ውኃው በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሲባረክ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳሽነት አማካይነት አዲስ የሆነ የመቀደስን ኃይል ገንዘብ ያደርጋል።”

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

- “እንዴት ያለ እንግዳና ለማሰብ የሚደንቅ ነገር ነው! [ለመጠመቅ ወደ መጠመቂያው ውኃ ስንገባ] ሞትን በአማናዊ ሁኔታ በተግባር አልተቀበልንም፣ በእውነትም አልተቀበርንም፣ አልተሰቀልንም፣ ሞተንም አልተነሣንም፤ እነዚህን ሁሉ የተሳተፍነው በምሳሌ ነው እንጂ፤ የምናገኘው መዳን ግን እንደምንሳተፍበት መንገድ ምሳሌያዊ ሳይሆን አማናዊ ነው።

- “ክርስቶስ በእውነት ተሰቅሏል፣ በእውነት ወደ መቃብር ወርዶ ተቀብሯል፣ ከዚያም በእውነት ተነሥቷል፤ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እኛ በምሳሌ ተሳትፈን መዳንን ግን በእውነት እናገኝ ዘንድ በነጻ በቸርነቱ ሰጥቶናል።
- “ምን ዓይነት ዕፁብ ድንቅ የሆነ ሰውን መውደድና ቸርነት ነው! ክርስቶስ ንጹሐት በሆኑ እጆቹ ላይ በችንካር ተቸነከረ፣

- “ሕማማትንም ተቀበለ፤ በእኔ ግን ያለ መቸንከርና ያለ ሕማምና ጭንቅ በእርሱ የደረሰው ችንካርና ሕማም ሳይደርስብኝ እንዲሁ ሕማሙን በማመንና በምሳሌ በመሳተፍ [ወደ ውኃው በመግባትና በመውጣት ሞቱንና ትንሣኤውን በመመስከርና በመሳተፍ] መዳንን በነጻ ሰጠኝ።”

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

- “በጥምቀት የመለኮታዊ ኃይል መገኘት በፈራሽ ባሕርይ የተወለደውን ወዳለመፍረስና ወዳለመለወጥ ከፍ ያደርገዋል። ከመዋቲነትና ከፈራሽነት መውጣትና ወደ ዘለዓለማዊነትና ሕያውነት ማለፍ የሚቻለው ክርስቶስን በጥምቀት በመምሰልና በመከተል ብቻ ነው።”

ቅ. ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ

# ፪. ምሥጢረ ሜሮን

- መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው በውኃ አማካይነት በሚፈጸም ምሥጢረ ጥምቀት ልጅነትን፣ ሥርየተ ኃጢአትን . . . ይሰጠናል፤ በቅብዐ ሜሮን አማካኝነትም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ያሳድርብናል፣ ያትመናል።
- በጥምቀት ጊዜ በጸሎት በሚከብረው ማየ ጥምቀቱ (ውኃው) ምክንያት (የሚታይ መሣሪያ) ሲሆን ዳግም የምንወለደው ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ሁሉ በቅብዐ ሜሮንም የሚቀባው ሰው አካሉ ላይ የተቀደሰው ቅባት (ሜሮን) ሲያርፍ መንፈስ ቅዱስ በዚያ አማካይነት ያከብረዋል፣ ያትመዋል።

- “እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ። . . . እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፣ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም። ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፤ እውነተኛም እንደ ሆነ፣ ውሸትም እንዳልሆነ፣ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ።”

1 ዮሐ. 2:20 ፣ 21 ፣ 27

# ምሥጢረ ሜሮን በአበው ሊቃውንት ትምህርት

- “ልብስህን ባወለቅህና ዕራቁትህን በሆንህ ጊዜ በተቀደሰው ቅባት (በሜሮን - μύρῳ) ተቀባህ፤ ከራስህ ጸጉር አንስቶ እስከ እግርህ ድረስ ተቀባህ፤ . . . የተቀደሰው ቅባት (ሜሮን - μύρῳ) ብዙ ከሆነው ከክርስቶስ ሀብታት የመካፈል ምልክት ነው። የቅዱሳን እስትንፋስና የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ልክ በላዒ እንደ ሆነ ኃይለኛ የእሳት ነበልባል ርኩሳን መናፍስትን እንደሚያቃጥላቸውና እንደሚያባርራቸው ሁሉ፤

- እንደዚሁም በጸሎት የተባረከው (የከበረው) ቅባት (ሜሮን - μύρῳ) ስመ እግዚአብሔርን በመጥራትና በጸሎት የኃጢአትን ቅሬት ማቃጠልና ማንጻት ብቻ ሳይሆን የክፉውን መንፈስ ረቂቅና የማይታዩ ኃይላት ሁሉ የማባረር ኃይልን ያስገኛል።”
- ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 3

- “ይህ ሜሮን ተራ ቅባት ነው ብለህ እንዳታስብ ተጠንቀቅ። ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በመሥዋዕቱ ላይ እንዲወርድና መሥዋዕቱን እንዲያከብረው በጸሎተ ቅዳሴው ከተጠራና ካከበረው በኋላ የቁርባኑ ኅብስት መጀመሪያ እንደ ነበረው ተራ ኅብስት ሳይሆን የራሱ የክርስቶስ ሥጋ እንደሚሆን ሁሉ ይህ ቅዱስ ቅባትም ተራ ቅባት አይደለም፣

- “በጸሎት ከከበረ በኋላ የክርስቶስን የጸጋ ስጦታ የሚያሳድርና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጸጋውን ለማሳደር ተገቢ የሆነ መሣሪያ ይሆናል እንጂ። ይህ ቅባትም በግምባራችን ላይና በሌሎች የሰውነታችን አካላት ላይ ይደረጋል፤ የሚታየው ሰውነት በሚታየው በከበረው ቅባት (በሜሮን) ሲቀባ ነፍስ ደግሞ ቅዱስና ሕይወት ሰጭ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ትቀደሳለች።

- “መጀመሪያ ሜሮኑን ከግምባራችሁ ላይ ተቀባችሁ (ታተማችሁ)፣ ሕገ እግዚአብሔርን ያፈረሰው የመጀመሪያው ሰው (አዳም) በየሄደበት ሁሉ ተሸክሞት ይዞር ከነበረው ኃፍረት ነጻ ትሆኑ ዘንድ፤ እንዲሁም *በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመሰል ዘንድ* (2 ቆሮ. 3፡18)።

- “ከዚያም በጆሯችሁ ላይ ተቀባችሁ፣ አምላካዊ ምሥጢራትን ለመስማት የፈጠኑ ጆሮዎችን ትቀበሉ ዘንድ፤ ኢሳይያስ “እግዚአብሔር ሆይ፣ የሚሰማ ጆሮን ሰጠኝ” እንዳለው ያለ እንዲሁም ጌታችን “ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ” እንዳለው ያለ ጆሮን እንቀበል ዘንድ። ኢሳ. 50፡4 ማቴ. 11፡15 ቀጥሎም አፍንጫ ላይ ተቀባህ፤ ይህም የተቀደሰውን ቅባት ስትቀባ “በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና” ማለት የምትችል ትሆን ዘንድ ነው። 2 ቆሮ. 2፡15

- “በመቀጠልም ጡታችሁ ላይ ትቀባለችሁ፤ ይህም ‘የጽድቅንም ጥሩር ለብሰህ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወም ዘንድ’ እንድትችል ነው። ኤፌ. 6፡11፣ 14 ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ መሰጠት በኋላ ጠላትን ድል እንዳደረጉት ሁሉ እንደዚሁም ከቅዱስ ጥምቀት እና ከምሥጢራዊው ሜሮን በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ዕቃ ጦር ሁሉ ለብሰን በጠላት ኃይል ላይ ልንነሣበትና ‘ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ’ እያልን ድል ልናደርገው ይገባል። ፊል. 4፡13”

**ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም**

# ፫. ምሥጢረ ቁርባን

- “እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ ... የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም። ...

- “የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፣ ሰው ከእርሱ በልቶ አንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።”

ዮሐ. 6:26-27 ፣ 35:49-51

S

- “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመሰግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎችም ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።”

ማቴ. 26:26-28

- S

# 1) የዘላለም ሕይወት

- “ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

## ዮሐ. 6፡53-56

# 2) ከክርስቶስ ጋር እንዋሐዳለን

- “ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።”

  ዮሐ. 6፡53-56

# 3) የኃጢአት ይቅርታ እናገኛለን

- “ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎችም ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።” ማቴ. 26:26-28
- “ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።”

1 ዮሐ. 1:7

# 4) ሞቱንና ትንሣኤውን እናስባለን፣ እንመሰክራለን

- “ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።”

1 ቆሮ. 11:26

# 5) ኃጢአትን ለማሸነፍ ኃይልና ጉልበት እናገኛለን

- “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።”

## ፊል. 4፡13

- “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።” ገላ. 2፡20

ም. ቁርባን ራሱ በጸሎተ ሐሙስ ጌታ የፈጸመው ምሥጢር ነው። በየቅዳሴው ጊዜ የሚፈጸመው ያው ምሥጢር ነው። የሚደጋገም አይደለም፣ ያው ራሱ የምሴተ ሐሙሱ፣ ጌታ በዕለት ዓርብ የፈጸመው ነው እንጂ።

# ምሥጢረ ቁርባን በአበው ትምህርት

- “. . . ሀበነ ሥጋከ ወደመከ ዘወሀብኮሙ ለአርዳኢከ . . . ኅብስተ ሕይወት ኅብስተ መድኃኒት ዘወረደ እምሰማያት በዘይሠረይ ኃጢአት . . . - ለደቀ መዛሙርትህ እንደ ሰጠሃቸው ለእኛም ቅዱስ ሥጋህንና ክቡር ደምህን ስጠን፣ . . . ኃጢአት በሚሠረይበት ገንዘብ ከሰማያት የወረደ የሕይወት ኅብስትና መድኃኒት ነው . . .”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ ቴዎድሮስ)

- “ከቅዱስ ቁርባንና ከጸሎት ይርቃሉ፤ ምክንያቱም በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርበው ኅብስት ስለ እኛ ኃጢአት መከራ የተቀበለውና ከሞት የተነሣው የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መሆኑን አያምኑምና ነው። ስለዚህ በዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የማይገባ ነገር የሚናገሩ ሰዎች እነርሱ በክርክራቸው መካከል ሞትን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ (እየተከራከሩ ሳሉ ይሞታሉ)።

- “ወረደ ወልድ እምሰማያት ወተወልደ በተድላ መለኰት ወቦአ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወቦአ ውስተ ይእቲ ማዕድ ደመረ ሥጋሁ ውስተ ዝንቱ ኅብስት ወከዓወ ደሞ ውስተ ዝንቱ ጽዋዐ መድኃኒት ወዲያቆንሰ ዘንተ ርእዮ አንከረ ሀለው ካህናት ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ እምዝንቱ ኅብስት ወ. ወሀቡ ለሕዝብ እንዘ ትብሉ ሥጋሁ ለክርስቶስ አሜን ይበል ዘይትሜጦ ወ. ዘኒ ጽዋዐ ሀቡ እንዘ ትብሉ ደሙ ለክርስቶስ አሜን አሜን ይበል ካዕበ ዘይትሜጦ ወ. መንክር ግብር ወዕፁብ ዘተገብረ ሥጋሁ ቅዱስ መብልዓ ጽድቅ ለሰብእ ዘረሰዮ ለሥርየተ ኃጢአት . . . - ወልድ ከሰማያት ወረደ፣ በመለኰት ክብር ተወለደ፣ ወደ መጋረጃው ውስጥም ገባ፣

- ወደዚህች ማዕድም ገባ፣ ሥጋውን ከዚህ ኅብስት ጋር አንድ አደረገ፣ ደሙንም በዚህ በመድኃኒት ጽዋ ውስጥ አፈሰሰ (ጨመረ)፤ ይህን የተመለከተ ዲያቆንም [ቅዱስ እስጢፋኖስ] አደነቀ። ካህናት በመጋረጃው ውስጥ አሉ፤ እነርሱንም ጌታችን እንዲህ አላቸው፡- ‘ከዚህ ኅብስት ብሉ፣ ለሕዝቡም ‘ይህ የክርስቶስ ሥጋ’ ነው እያላችሁ ስጡ፤ ሥጋውን የሚቀበለውም ‘አሜን’ ብሎ ይቀበል። ይህን ጽዋም (ደሙን) ‘ይህ የክርስቶስ ደም ነው’ እያላችሁ ስጡ፣ የሚቀበለውም ‘አሜን አሜን’ ብሎ ይቀበል። እጅግ በጣም አስደናቂና አስገራሚ ነገር ተደረገ፤ ይኸውም ቅዱስ ሥጋው ለሰዎች እውነተኛ ምግብና የኃጢአታቸው ማስተሥረያ መድኃኒት ሆኖ የመሰጠቱ ነገር ነው።”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

- “ነገር ግን በአክብሮት ቢመለከቱትና ቢያምኑበት ይሻላቸው ነበር። ስለዚህ እንደዚህ ካሉት ሰዎች ትርቁ ዘንድ የተገባ ነው፣ ከእነርሱ ጋርም በግልም ሆነ በማኅበር ግንኙነት አይኑራችሁ።”

ቅዱስ አግናጥዮስ

- “ታላቁ ጸሎትና አስተብቁዖታት ወደ እግዚአብሔር ከተደረገ በኋላ ቃል በኅብስቱና በጽዋው ላይ ይመጣል፣ እነርሱም [ኅብስቱና በጽዋው ያለው ወይን] የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ደም ይሆናሉ።” ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ

- “በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርቡት ኅብስቱና ወይኑ ቅዱስና ገናና የሆነውን ስመ ሥላሴን ከመጥራታችንና ከመማጸናችን በፊት ተራ ኅብስትና ወይን እንደ ነበሩ ሁሉ፣ ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ግን ኅብስቱ የክርስቶስ አካል ይሆናል፣ ደሙም የክርስቶስ ደም ይሆናል።”

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

- “. . . እጅግ የተከበርህ ወዳጄ ሆይ፣ እግዚአብሔር ቃልን በጸሎትህ ስትጠራውና ያለ ሥለት በሆነ ሁኔታ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በምትፈትትበት ጊዜ ስለ እኔ መጸለይንና መማለድን አታቋርጥ::”

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ጎበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ ዘኢቆንዮን

- “ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት ብቻ እንኳ እነዚያን አምላካውት ምሥጢራት በተመለከተ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች መሆን እንድትችሉ ለማድረግ በራሱ በቂ ነው። ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ሰምታችሁታልና፡- ‘ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ ይህ ደሜ ነው፣ እንካችሁ ጠጡ አላቸው።’ እንግዲህ እርሱ ራሱ ባለቤቱ ጎብስቱን *‘ይህ ሥጋዬ ነው’* ብሎ ከተናገረና ካወጀ ይህን ሊጠራጠር የሚችል ማን አለ? እንዲሁም እርሱው ራሱ በማይታበል ቃሉ *‘ይህ ደሜ ነው’* ብሎ በግልጽ የተናገረውን ‘አይ የእርሱ ደም አይደለም’ ብሎ ማን ሊያመነታና ሊጠራጠር ይችላል? **ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም**

# መሥዋዕት

- ስለሆነም በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የሚቀርበው መሥዋዕት ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት ሳይሆን ጌታችን አንድ ጊዜ የፈጸመውና በዕለተ ዓርብ የቆረሰው ሥጋውና ያፈሰሰው ደሙ ነው፤ በየጊዜው በየቤተ ክርስቲያኑ በጸሎተ አኮቴት የሚከብረውና የሚለወጠው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከዚያች ከዕለተ ዓርብ ጋር የሚገናኝና አንድ የሚሆን ነው ማለት ነው።
- የእያንዳንዱ ጸሎተ ቅዳሴ ፈጻሚውና ቀዳሹም ራሱ ጌታችን ነው።

- 23 እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፥ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና፤

- “እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና። ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና፤ ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ይሾማል።”

- ዕብ. 7፡23-28

- “እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም። እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉቱ ራሳቸው ከእርሱ ይልቅ በሚበልጥ መስዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ። ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች፥ የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ።

- “ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፤ እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፥ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፥ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።”
- ዕብ. 9፡25-28

- 10 በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል። ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥

- “. . . የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም።

ዕብ. 10፡10-12፣ 18

16 ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።

17 ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

18 ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤

19 እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።

20 እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።

# የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በቀደምት አበው ትምህርት

“ሀበነ ንንሣእ ወንትመጦ እምዝንቱ ኅብስት ሥጋከ ውእቱ ዘወረደ እምሰማያት ዘሐዳስ ሥርዓት . . . - የሐዲስ ሥርዓት መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ከሰማይ የወረደውንና ቅዱስ ሥጋህ የሆነውን ይህን ኅብስት እንቀበል ዘንድ መስጠትን ስጠን”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአቡነ አረጋዊ)

- “ታዲያ ይህ ምንድን ነው? በየቀኑ መሥዋዕት አናቀርብምን? አዎ፣ በርግጥም እናቀርባለን፤ ሆኖም የምናቀርበው መሥዋዕት ሞቱን በማሰብ ነው፣ ይህ መሥዋዕትም አንድ ነው እንጂ ብዙ አይደለም። ብዙ ያይደለ አንድ የሚሆነው እንዴት ነው? ያ መሥዋዕት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደ ተሠዋና ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደ ገባ ይህም ያን ጊዜ ያቀረበውን መሥዋዕት ያንኑ ነው እንጂ ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት አይደለም።

- ሁል ጊዜ የምናቀርበው መሥዋዕት ያው አንድ ነው እንጂ ዛሬ አንድ በግ ነገ ደግሞ ሌላ በግ አይደለም፤ ሁል ጊዜ፣ ዛሬም ነገም አንድ ነው እንጂ፤ ስለዚህም መሥዋዕቱ ያው አንድ ነው። እንዲህ ሆኖም ግን አሁንም መሥዋዕቱ በተለያዩ ቦታዎች (ቤተ ክርስቲያናት) ስለሚቀርብ ብዙ ክርስቶሶች አሉን? በጭራሽ! በየትም ቢሆን ክርስቶስ አንድ ነው፤ እዚህም በፍጹም ሙሉነት በእርሱነቱ አለ፣ እዚያም እንዲሁ እርሱው ራሱ እንበለ ሕጸት አለ፣ አንድ አካል።

- ስለሆነም በተለያዩ ቦታዎች ቢሠዋም አንድ አካል ነው እንጂ ብዙ አካል እንዳይደለ ሁሉ፤ እንደዚሁም እርሱ አንድ መሥዋዕት ነው። እኛን የሚያነጻንን መሥዋዕት ያቀረበው ሊቀ ካህናታችን እርሱ ነው። እና ዛሬ የምናቀርበው መሥዋዕት ያን ጊዜ የቀረበውን መሥዋእት ነው፣ በየጊዜው ቢቀርብ አያልቅም። በየጊዜው የምናቀርበው መሥዋዕት ሌላ መሥዋዕት አይደለም፣ ሁል ጊዜ የምናቀርበው ያንኑ መስዋዕት ነው እንጂ።”

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን

“ጌታችን ተሰውቶ በምሥዋዑ (በታቦቱ) ላይ ተኝቶ ስታየው፣ ካህኑ ቆሞ በመሥዋዕቱ ላይ እየጸለየ ስትመለከተው፣ ምእመናን ሁሉ በዚያ በከበረው ደሙ እየተነዙ ስታይ፣ ከሰዎች መካከል እንዳለህ ታስባለህን? በምድር ላይ ያለህ ይመስልሃን?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፣ መጽሐፍ 4

- “አሁንም ያው በጸሎተ ሐሙስ ጌታችን ራሱ የፈጸመው መሆኑን እመን፤ ይህ እኛ የምናከብረው መሥዋዕት ከዚያ [በጸሎተ ሐሙስ ጊዜ ከነበረው] በምንም ምን የተለየ አይደለምና። ይህን ሌላ ሰው የሚፈጽመው፣ ያን ግን እርሱ ራሱ የፈጸመው አይደለምና፣ ይህም ያም ሁለቱም የእርሱ ሥራዎች ናቸው እንጂ። ስለዚህ ካህኑ እጁን ዘርግቶ ለአንተ ሲያቀብልህ ስታይ የሚያደርገው ካህኑ ነው ብለህ አታስብ፣ ወደ አንተ የተዘረጋው የክርስቶስ እጅ ነው እንጂ።

- “ያን ጊዜ በምሴተ ሐሙስ ያደረገው እርሱ አሁንም መሥዋዕቱን የሚያከብረው እርሱ ራሱ ነው። እኛ አገልጋዮች ነን። መሥዋዕቱን የሚቀድሳቸውና የሚለውጣቸው ያው አንድ እርሱው ነው። ይህ መሥዋዕትም እንደ ጸሎተ ሐሙሱ ያው ነው፣ በአንዳችም ነገር ያነሰና የተለየ ነገር የለውም። ያን (የጸሎተ ሐሙሱን) ያከበረውና የፈጸመው ክርስቶስ፣ ይኽን ግን ሰው አይደለም፤ ይኽንም የሚያከብረውና የሚለውጠው እርሱ ነው እንጂ።

- ይህ (ቤተ ክርስቲያን) ጌታችን ከሐዋርያቱ ጋር እንደ ነበረበት ቤት ነው። ያን መሥዋዕት ያከበረው ክርስቶስ ይህንም የሚያከብረው እርሱው ነው። . . . ቆሞ የሚታየውና የሚላላከው ካህኑ ነው፣ ኃይሉና ጸጋው ግን የእግዚአብሔር ነው።”

*ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ*

# ስብሐት ለእግዚአብሔር